# ፖሊሲ JLCB- የተማሪዎች ክትባት

ተማሪው በጤና፣ ሀይማኖታዊ፣ ግላዊ ወይም ህግ እንዳስቀመጠው በሌሎች ምክንያቶች ነጻ ካልሆነ በስተቀር፣ ህጋዊ የክትባት ግዴታዎችን ያላሟላ አንዳችም ተማሪ በዚህ ዲስትሪክት ውስጥ እንዲማር ወይ ትምህርቱ እንዲቀጥል አይፈቀድለትም።

የክትባት ምስክር ወረቀት ወይም ከክትባቱ ነጻ የሚያደርጋቸው ህጋዊ ምክንያት ያላቀረቡ ተማሪዎች፣ ነጻ የሚያደርጋቸው ምስክር ወረቀት እስከሚያቀርቡ ድረስ ከትምህርት ገበታቸው ይታገዳሉ ወይም ከነአካቴው ይባረራሉ።

አስተዳደሩ ከህጉ ጋር የሚጣጣሙ ደንቦችን በሥራ ላይ ያውላል።

የወቅታዊ አሰራር ደንብ የወጣው 1993
የጸደቀው፥ መመሪያው የጸደቀ ቀን

ሕጋዊ ዋቢዎች፥

C.R.S. 22-33-106
C.R.S. 25-4-901 *et seq.*
6 CCR 1009-2

ተዛማጅ ማጣቀሻዎች፥

JFC፣ የተማሪ ወደ ትምህርት ቤት መግባት እና ከትምህርት ቤት ማቋረጥ

JHD፣ ከትምህርት ቤት መወገድ እና ላለመገኘት በይለፈኝ መታለፍ

JKD/JKE፣የተማሪ እገዳ/መባረር

JRA፣ የተማሪ ሪኮርዶች

# የኮሎራዶ እስቴት

John W. Hickenlooper, ገቨር ነር
Christopher E. Urbina, MD, MPH
ውሳኔ ሰጪ ዳሬክተር እና የጤና አዛዥ መሪ ሰራተኛ

የኮሎራዶን ህብረተሰብ እና የአካባቢውን ጤንነት ለመከላከል እና ለመጠበቅ

4300 Cherry Creek Dr. S.
Denver, Colorado 80246-1530
Phone (303) 692-2000
በኮሎራዶ በGlendale፣ይገኛል

Lየላቭራቶሪ አገልግሎት ክፍል
8100 Lowry Blvd.
Denver, Colorado 80230-6928
(303) 692-3090

Colorado Department
of Public Health
and Environment

http://www.cdphe.state.co.us

ጥር 10, 2013

በኮሎራዶ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆች፣ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (የትምህርት ዓመት 201-14)፣

ክትባት የልጆቻችንን ጤና መጠበቂያ ከሆኑት ጠቃሚ ነገሮች አንዱ ነው እና ትምህርት ቤት የሚሄዱ ልጆች በክትባት የሚከለከሉትን በሽታዎች ለመከላከል እንዳለባቸው የኮሎራዶ ህግ ይፈልጋል። የዚህ ደብዳቤ ዓላማ ክትባቶች ለትምህርት ቤት ክትትል እንደሚያስፈልጉና በክትባት የሚከለከሉትን በሽታዎች ለመከላከል የትኛዎቹ **ክትባቶች** መጠቀም እንደሚያስፈልግ **የተሰጠውን ሃሳብ** ለማሳወቅ ነው （ በገጽ 2 ያለውን ሰንጠራዥ ይመልከቱ） ።

ወላጅ እንደመሆንዎ መጠን፣በኮሎራዶ እስቴት በት/ቤት መግቢያ የጤና ቦርድ ተፈላጊ ከሆኑት ክትባቶች በተጨማሪ፣በክትባት ልምዶች ላይ የመማክርት ኮሚቴ（Advisory Committee on Immunization Practices (ACIP)）የተመከሩትን ክትባቶችን ማወቁ ጠቃሚ ነው። ይህ ልጅዎን በክትባት የሚከለከሉትን በሽታዎች ለመከላከል የበለጠውን ጠቃሚ የሆነ የክትባት መርኃ ግብር ነው።

ወላጆች በልጆች ክትባትና የክትባት ደህንነት ላይ ያሳስባቸዋል ወይም የበለጠውን መረጃ ይፈልጋሉ። ስለ ክትባቶች ደህንነትና ጠቀሜታ በተመለከተ ዘወትር ስለሚጠየቁ ጥያቄዎች ለወላጆች የተዘጋጀ ምንጭ በ: www.ImmunizeForGood.com ይገኛል። የኮሎራዶ የክትባት ድህረ ገጽ በ: www.ColoradoImmunizations.com ይገኛል።

ት/ቤቶች ለክትባት ህጎች ተገዢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በትጋት ይሠራሉ። በት/ቤት ምዝገባ ወቅት ወቅታዊውን የክትባትና ልጅዎ ተጨማሪ ክትባት ሲወስድ ማስረጃ በማቅረብ ለሚያደርጉት ዕርዳታ እናመሰግንዎታለን። *እባክዎን የልጅዎን ክትባት ፍላጎቶች ከልጅዎ ሀኪም ወይም ከአካባቢ የህዝብ ጤና ድርጅት ጋር ይወያዩ።* *（የአካባቢ የህዝብ ጤና ድርጅት መገናኛ መረጃ ለማግኘት ለቤተሰብ ጤና መስመር በ*1-303-692-2229 ወይም 1-800-688-7777 ይደውሉ። እባክዎን ልጅዎ ክትባት በሚወስድበት በያንዳንዱ ጊዜ የ ልጅዎን አዲሱን የክትባት ማስረጃ ያምጡ።

በትህትና፣

የኮሎራዶ የክትባት መርኃ ግብር （Colorado Immunization Program）
Colorado Department of Public Health and Environment
303-692-2650

ለክትባት ማስረጃ **የሚያስፈልግ** ትንሹ መጠን

ከመዋዕለ ህጻናት እስከ ክፍል 12፣ለትቤት ክትትል ተፈላጊ ነው።

| ክትባት | የሚሰጠው መጠን ቁጥር | ክፍል K-12 (ዕድሜ ከ5-18 ዓመት) |
|---|---|---|
| | *ክትባቶች የሚሰጡት ≤ 4 ቀን፣በትንሹ የሚፈለገው ዕድሜ ከመሟላቱ ከፊት* | |
| **ፔርቱስስ （Pertussis）**<br>*DTaP እስከ 6 ዓመት ዕድሜ ላላቸው ልጆች ብቻ የተፈቀደ ነው።* | 5 እስከ 6 | 5 **DTaP** ( መጠን 4 በ4ኛ ወይም ከ4ኛ የልደት ቀን በኋላ ቢሰጥ መስፈርቱ ይሟላል)። የመጨረሻ የ DTaP መጠን 4 ዓመት ሳይሞለው በፊት መሰጠት የለበትም። **Tdap** ለ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች ይፈለጋል። |
| **የመንጋጋ ቆልፍ በሽታ(Tetanus/Diphtheria）**<br>*DT እስከ 6 ዓመት ዕድሜ ላላቸው ልጆች ብቻ የተፈቀደ ነው።* | 3 እስከ 5 | 5 **DT** ( መጠን 4 በ4ኛ ወይም ከ4ኛ የልደት ቀን በኋላ ቢሰጥ መስፈርቱ ይሟላል)። አንድ ልጅ 7 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ሲሆነው፣ በ3 ተገቢ ተርታ የሚሰጡ tetanus/diphtheria የሚይዙ ክትባቶች （DTaP፣ DT፣ Td፣ Tdap) ሊኖራቸው ይገባል - ከመጠን 1 እና 2 መካከል 4 ሳምንት እና በመጠን 2 እና 3 መካከል 6 ወራት። |
| **ፖሊዮ （Polio (IPV)）** | 3 እስከ 4 | 4 **IPV** ( መጠን 3 በ4ኛ ወይም ከ4ኛ የልደት ቀን በኋላ ቢሰጥ መስፈርቱ ይሟላል)። የመጨረሻ መጠን የ4 የልደት ቀን ሳይሞላ በፊት መሰጠት የለበትም። |
| ***ክፍኝ /እባጭ/ሩቤላ （MMR) Measles/Mumps/Rubella (MMR) ለዚህ የትምህርት ዘመን ምክር የተሰጠበት - የሩቤላ 1 መጠን መስፈርቱን ያሟላል።*** | 2 | የመጀመሪያ መጠን ከ1ኛ የልደት ቀን በፊት ከ4 ቀን በበለጠ ቀን ውስጥ አይሰጥም። ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል 2 መጠን ያስፈልጋል። |
| **ቨሪሴላ (Chickenpox)**<br>*ከጤና አጠባባቅ አቅራቢ （ሀኪም፣ነርስ ወይም የሀኪም ረዳት） በሽታ ለመኖሩ ማስረጃ መቅረብ አለበት።* | 1 ወይም 2 | የመጀመሪያ መጠን ከ1ኛ የልደት ቀን በፊት ከ4 ቀን በበለጠ ቀን ውስጥ አይሰጥም። ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል 2 መጠን ያስፈልጋል። ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል 2 መጠን ያስፈልጋል። ከ7ኛ እስከ 12ኛ ክፍል 1 መጠን ያስፈልጋል። |
| **Hepatitis B**<br>*ኦ ኤ ኦ ከጥር 7፣2009 በፊት የHep B 3 መጠን ያልወሰደ፣* በክትባት ልምዶች ላይ የመማከርት ኮሚቴ የተመከረውን ዝቅተኛውን የጊዜ ገደብ መከተል አለበት። | 3 | ሁለተኛ መጠን ቢያንስ ከመጀመሪያ መጠን ቢያንስ ከ4 ሳምንት በኋላ መሰጠት አለበት። ሦስተኛ መጠን ከመጀመሪያ መጠን ቢያንስ ከ16 ሳምንት በኋላ መሰጠት አለበት እና ከሁለተኛ መጠን ቢያንስ 8 ሳምንት። የመጨራሻ መጠን ከ24 ሳምንት （6 ወር በፊት መሰጠት የለበትም። የ2 - መጠን ተርታዎች ለዕድሜ 11-5 ተቀባይነት አላቸው። የ2 መጠን ተቀባይነት የሚያገኙት ተገቢ ሰነድ ኖሮ ለ2 መጠን ተርታ ፈቃድ ሲኖራቸው ብቻ ነው (የክትባቱ ስም፣መጠን፣ ቀናት፣እና የጊዜ ገደብ)። |

በክትባት ለሚከለከሉ በሽታዎች **የተመከሩ** ምርጥ መከላከያ የሚሆኑ ክትባቶች

| ክትባት | የሚሰጠው መጠን ቁጥር | ክፍል K-12 (ዕድሜ ከ5-18 ዓመት)<br>*ክትባቶች የሚሰጡት ≤ 4 ቀን፣በትንሹ የሚፈለገው ዕድሜ ከመሟላቱ ከፊት* |
|---|---|---|
| **ጉንፋን (Influenza (Flu)）** | 1 እስከ 2 | ዕድሜው ከ9 ዓመት በታች ከሆነ፣በያንዳንዱ መጠን መካከል ቢያንስ የ28 ቀን ክፍተት መኖር በመጀመሪያ 2 መጠን መሰጠት አለበት፣ከዚያም 1 መጠን በየዓመቱ። ዕድሜአቸው 6 ወር እና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ልጆች ያስፈልጋል። |
| **ማጅረት ገትር Meningococcal Meningitis (MCV)** | 1 እስከ 2 | ዕድሜአቸው ከ 11-18 ለሆናቸው ወጣቶች |
| **የሰው （Human ） Papillomavirus (HPV)** | 3 | ዕድሜአቸው ከ 11-18 ለሆናቸው ወጣቶች |
| **Hepatitis A (Hep A)** | 2 | ዕድሜአቸው 1 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ለሁሉም ልጆች ያስፈልጋል። |

**ለተፈላጊ** ክትባቶች፤ነጻ መሆን የሚያሳይ የለቦራቶሪ ውጤት በቂ ነ ው።

**ለህጉ ተገዢ ለመሆን ለልጆዎ ት/ቤት ከሚከተሉት አንዱን ማቅረብ አለብዎት፤**

1. ተፈላጊውን የመጨረሻ አነስተኛ ክትባቶችን ተማሪው መውሰዱን የሚያሳይ የተሟላ የክትባት ማረጋገጫ።
2. የተማሪው የክትባት ማረጋገጫ ያልታደሰ ከሆነ፣ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ነጻ የወጣው ተማሪ የሚቀጥለው ተፈላጊ ክትባት መሰጠቱን የሚያሳይ ማስረጃ ለማቅረብ ቀጥተኛ ማስታወቂያ ከተሰጠውና የማንኛውም ተጨማሪ ተፈላጊ ክትባቶች ማስረጃ ለማቅረብ 14 ቀን ይኖረዋል። ዕቅዱ ባይጠናቀቅ፣ለህጉ ተገዢ ባለመሆኑ፣ ተማሪው ይታገዳል ወይም ይበረራል። የክትባት እጥረት ካለ ይህ ህግ አስገዳጅ አይሆንም።

ከክትባት ነጻ የመሆን መግለጫ - የኮሎራዶ የህዝብ ጤናና እና የአካባቢ መምሪያ የክትባት ማረጋገጫ፣

a) ክትባት የተማሪውን አካላዊ ሁኔታ ህይወትና ጤና ለአደጋ የሚያጋልጥ ወይም በህክምና ተፈላጊ አለመሆኑን **የህክምና** ነጻነት ፈቃድ ካለው ሀኪም ሲያቀርብ፣ ወይም ፣
b) ክትባትን የሚቃረን ሃይማኖት እንዳለው ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ነጻ የወጣው ተማሪ በፎርማ የሚያረጋግጥ **የሃይማኖት ነጻነት**፣ወይም
c) ክትባትን የሚቃረን ሃይማኖት እንዳለው ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ነጻ የወጣው ተማሪ በፎርማ የሚያረጋግጥ **የግል ነጻነት**፣

***የክትባት ተፋላጊነት ለሁሉም ተማሪዎች በጥብቅ ተፈጻሚ ይደረጋል።*** በኮሎራዶ በተከለሰው ህግ 25-4-902መሠረት መስፈርቱን የማያሟሉ ተማሪዎች ትምህርት እንዳይከታተሉ ይከለከላሉ። ይከ

***በቤተሰብ የጤና መስመር ላይ ስለ ነጻ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ስላለው ክትባት በተመለከተ በ303-692-2229 ወይም 1-800-688-7777 ይደውሉ።***